# የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት
# The Coalition of Ethiopian Opposition Political Organizations (CEOPO)

*Y.CEOPO Postfach 102409, 60024 Frankfurt – Germany, e-Mail* **CEOPO@T...online.de** *TEL./FAX: +49-69 37108840*

የተከበራችሁ ወገኖቻችን

የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት ከሁሉ አስቀድሞ ይህ ጉባኤያችሁ
ውስብስብ በሆነው የሃገራችን ሁኔታ በጥሞና ተወያይቶ ለቀጣዩ የጋራ ትግላችን አንድ ጥ
ራት ያለው የጋራ ስትራቴጂ ለመቀየስ የሚያስችል ጉባኤ እንዲሆን ያለውን ምኞትና ተስፋ
ሊገልጽላችሁ ይወዳል::

ኢተፖድህ ባለፈው መስከረም ወር በፍራንክፈርት ከተማ ባደረገው ሁለተኛ ጠቅላላ
ጉባኤ የሚቻሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ ለምርጫው እንቅስቃሴ /ወይም ካምፔይን/ ተመዝግበ
ው እንዲሳተፉ ጥሪ ሲያደርግ በዚህ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ከዳር እስከዳር ከሚቆጣ
ጠረው የምርጫ ሂደት ለተወሰኑ ተቃዋሚያች ወያኔ/ኢህአዴግ ወደና ፈቅደ ለሚለቃቸው ጥቂ
ት የፖርላሜንት ወንበሮች ለመዋደቅ ሳይሆን በዚህ የምርጫ እንቅስቃሴ ባቢያ አንድ የህ
ዝባዊ ትግል አዲስ እመርታ ለመቀስቀስ የሚቻልበት ሁኔታ ለማመቻቸት እንደሆነ በተደጋጋ
ሚ ተገልጿል::

ዛሬ ሃገራችን ከዛሬ ስምንት ወር ይልቅ ዴሞክራቲክ አይደለችም:: ነገር ግን
ዛሬ በሃገራችን የዛሬ ስምንት ወር ያልነበረ ማንም ሊንቀው የማይችለው ዴሞክራሲያዊ ህ
ዝባዊ እንቅስቃሴ አለ:: ይህ ሁኔታ እንዲከሰት ዛሬ በዚህ አዳራሽ የምትገኙ ወገኖቻች
ን፣ ሌሎች በመሃከላችሁ የሌሉ ታጋዮችና በጠቅላላው ለፍትህና ለዴሞክራሲ ያለውን ጥማት
ለማርካት ሲዋደቅ ለአስብሪተኛ ካድሬያች ግፍ የተጋለጠው ህዝባችን ከፍተኛ መስዋእት ያደ
ረገ መሆኑ ማንም የሚክደው አይደለም::

በኢተፖድህ በኩል ይህ ጉባኤ እንዲጠራ በብርቱ የተደከመበት ዋናው ምክንያት ሌ
ላ ምንም ሳይሆን ይህ ባለፈት ወራት በከፍተኛ መስዋእትነት የተቀጣጠለው የህዝብ ትግል
ጋብ ካለ ቀስ በቀስ የሚከስምበት አደጋ ስለሚኖር እመርታው እንዲቀጥል ባለው ላይ ለመ
ገንባት የሚቻልበትን ዘዴ ተወያይታችሁና ተወያይተን ወደ ህዝባዊ ድል በጋራ የምንጓዝበ
ትን ጉዳና ለመቀየስ በማሰብ ነው::

ትግላችን በጋራ እንዲቀጥል በዚህ የወያኔ/ኢህአዴግ የምርጫ ሂደት ምንነት አን
ዱ ግልጽና በምንም ዓይነት አሻሚነት የሌለው አቋም እንዲኖረን ያስፈልጋል:: በሃገራችን
የምርጫ ተብዩ ሂደቶች ታሪክ የግንቦትን ሂደት የተለየ የሚያደርገው ለመጀመሪያ ጊዜ የህ
ይወት መስዋእት የተከፈለበት፣ ህዝብ የታሰረበት፣ የተንገላታበት፣ ቤት ንብረት የተቃጠ
ለበት፣ ሠራተኛ ከሥራ ገበሬ ከመሬቱ የተፈናቀለበት ባጭሩ ጸረ ህዝብ አፈናና ህዝባዊ ተ
ጋድሎ ተያይዘው ያደጉበት የትግል ሂደት መሆኑ ነው:: ይህም ሆኖ ዛሬም ቢሆን የኢትዮ

ጵያ ህዝብ አማራጭ ቀርቦለት ለመምረጥ ያለውን መብት ለማስከበር ተዋደቀ እንጂ አማራጭ አልቀረበለትም:: የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች ያላቸውን ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ህልም ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማስረዳት እንደልባቸው ለመንቀሳቀስ ያላቸው መብት እንዲከበር ተዋደቁ እንጂ ይህ መሰረታዊ መብታቸው አልተከበረም:: ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጎች ያሻቸውን ዜጋ ደግፈው ያሻቸውን ዜጋ ተቃውመው አቋማቸውን ለመግለጽ ያላቸው መብት እንዲከበር ታገሉ እንጂ ይህ መብታቸው አልተከበረላቸውም:: ባጭሩ በማንኛውም መስፈርት ቢኬድ በሃገራችን ነጻ፣ ርትአዊና ሃቀኛ ምርጫ አልተደረገም:: ይህ መሠረታዊ ሃቅ በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ በይፋ ካልተረጋገጠ ካለፈው ይልቅ ትንሽ ወንበሮች ለመልቀቅ የፈቀደው የኢህአዴግ መንግሥት ነጻ ምርጫ ተካሂዷል ብሎ ለመንዛት ለሚያስበው ሰፊ የአጥፊ ፕሮፖጋንዳ በር ስለሚከፍት ይህንን የወያኔ ሤራ ሙሉ በሙሉ ለማክሸፍ የዚህን የሽፍጥ ሂደት ምንነት ይህ ጉባኤ በምንም ዓይነት በማያወላዳ ሁኔታ እንዲያጋልጠው አደራ እንላለን::

ነገር ግን ትግላችን ሂደቱን የማጋለጥ ትግል ብቻ አይሆንም:: በመስዋእትነት በተገኘው ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ የትግል እንቅስቃሴ ላይ የመገንባትም ትግል ነው:: ይህ በምርጫው እንቅስቃሴ ሳቢያም ሆነ ከሱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት በሌላቸው ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ዙሪያ የተነሳሳው ህዝባዊ እንቅስቃሴ እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ ተብሎ በቀጠሮ የሚሸኝ እንቅስቃሴ መሆን የለበትም:: ሞሜንተሙን ጠብቆ መፋፋም፣ መቀጠል ይኖርበታል:: ለዚህ ደግሞ በንቅናቄው ስፋት፣ አገር አቀፋዊነትና ኃያልነት ከመዝናናት አልፍ ድክመቶችን አብጠርጥሮ ማውጣትንና እነሱንም ለመወጣት ያላሰለሰ ትግል ማካሄድን ይጠይቃል::

ትግሉ አንድ ዲሞክራቲክ ዓላማ ያለው ትግል ነው:: ትግሉ አንድ ጸረ ዲሞክራቲክ አገዛዝን ዒላማ አርጎ የተነሳሳ ትግል ነው:: ነገር ግን ቅንብርና ትግግዝ እንደሌለው በግልጽ ለማየት ተችሏል:: ይህ የቅንብርና የትግግዝ ዓላማ እስካሁን አስፈላጊው ትኩረት ስላልተሰጠው በሃገራችን ለፍትህ ለዲሞክራሲ ለህዝቦች አንድነትና ወንድማማችነት የሚደረገው ትግል በድርጅት፣ በብሄር፣ በአካባቢና በሙያ አጥሮች ጀርባ እንዲሰጣጥ የተደረገበት ሁኔታ ይታያል::

የአንዱ ትግል ለሌላው ጀርባ እየሰጠ በያለበት የየብቻው ትግል ከቀጠለ ከአዲስ አበባ እስከወረዳና መንደር ድረስ በተዋቀረና በተቀነባበረ ጸረ ህዝብ መዋቅር ለየብቻ የሚደመሰስበት አደገኛ ሁኔታ እንዳለ ለሁላችንም ግልጽ ይመስለናል:: ትግላችን ይህንን ችግር ባስቸኳይ እንዲወጣ ድርጅቴ ይቀድማል የሚሉ ኃይሎች አንድ ድርጅት ማንም ይሁን ማን የዚችን አገር ችግሮች ብቻውን ሊወጣ እንደማይችል እንዲገነዘቡ ያስፈልጋል:: ብሄሬን ብቻ የሚል ታጋይ ካለ ማንም ብሄር ብቻውን የወያኔን ጸረ ብሄር አቋም አሸንፎ ለራሱ ብቻ መብትና ነጻነት ሊያመጣ እንደማይችል መገንዘብ ይኖርበታል:: ሁላችንም የምንመኘው የኢትዮጵያ አንድነት በጽኑ መሠረት ላይ እንዲገነባ ከተነሳን በዚች የወያኔ/ኢህአዴግ የአናክሰህ ግዛ ፖለቲካ እየተፈታተናት ባለች አገራችን አንድነት ማለት ዛሬ የህዝቦች የትግል አንድነት እንደሆነ ሁላችንም እንድንገነዘብ ያስፈልጋል::

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ ዛሬ ለትግሉ ቀጣይነት ሲባል አንገብጋቢ አርገን የምንወስደው ተግባር የዚህ ትግል መቀነባበር ተግባር ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ጉባኤ በርግጥ ታሪካዊ ሊሆን የሚችለው ዛሬ በሃገራችን ያለው ታላቅ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ከመክሰም የሚድንበትን የመተባበርና የመቀነባበር ሁኔታ ለማመቻቸት አስፈላጊ የሆነውን ስልት ከነደፈ ብቻ ነው::

ትግሉ በሃገር አቀፍ ደረጃ መቀነባበር ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥና በውጭም የሚተባበርበት ሂደት መቀየስ ይኖርበታል:: ኢተፖድህ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚጠበቅበትን ማንኛውንም ሃላፊነት ለመወጣት ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ዝግጁ መሆኑን እየገለጸ የአገር ውስጡን ትግል ለማቀነባበርም ሆነ የውስጡን ከውጭ ለማስተባበር በሚደረገው ጥረት ሁሉ በአገር ውስጥ የኢተፖድህ ቀርንጫፍ ጽ/ቤት ከሚመለከታቸው ወገኖቻችን ጋር ሙሉ ትብብር እንዲያደርግ መመሪያ የተላለፈለት ስለሆነ የጉባኤው ተሳታፊዎች ይህንን በመረዳት ስለመ ጭው የጋራ ትግላችን ያላቸውን ማንኛውንም ሃሳብና አቋም በጽ/ቤታችን በ ኩል ቢያስተላልፉልን በሚቀጥለው ወር በሚደረገው የኢተፖድህ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ልዩ ት ኩረት ሰጥተን የምናስተናግድ መሆናችንን ከወዲሁ እንገልጸላችኋለን::

በመጨረሻም ይችን አጭር መልእክት ከመደምደማችን በፊት ባለፈት ወራት እንደ ማንኛውም ህዝብ የኢትዮጵያም ህዝብ የነጻ፣ ርትእዊና ሃቀኛ ምርጫ መብት ይረጋገጥለት ብለው ሲታገሉ ለተሰውት ወገኖቻችን ትግላቸው እንደሚቀጥል ለማረጋገጥ ለአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት እንድንነሳ በትህትና እንጠይቃለን::

የኢተፖድህ ሴክሬታር የት
ፍራንክፈርት /ጀርመን
የካቲት 27 ቀን 1992 ዓ.ም.